# RAPIDRIDE RAINIER LINE

Spring 2018

# ከዳውንታወን ሲያትል ወደ ማውንት ቤከር ከዛ ወደ ሬኒየር ቢች

## የሬኒየር መንገድን በሬኒየር አቨኑ ሳውዝ በመቀየስ እና የአውቶቢስ አገልግሎትን በማሻሻልይርዱን

እስከ 2021 ድረስ የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ 7 ቁጥር ወደ ራፒድ ራይድ ያድጋል! አዲሱ የሬኒየር መስመር ራፒድ ራይድ ላይን ዳውንታወን ሲያትልን ቻይናታወን፡ ኢንተርናሺናል ዲስትሪክትንና ሬኒየር ቢችን በሬኒየር አቨኑ ሳውዝ ላይ ያገናኛል፤፤ ይሚከተሉትን በማድረግ የሬኒየር መስመር ራፒድ ራይድ ላይን ህዝቡን ያጓጉዛል:

- አውቶቢሶችን ፈጣንና አስተማማኝ በማድረግ
- ተጨማሪ አውቶቢሶችን ለማታና ቅዳሜ፡እሁድ በማቅረብ
- የአውቶቢስ ፌርማታዎች ላይ መብራት፤ መምጫ ሰዓት የሚያሳይ መሳሪያና ሌሎች ነገሮችን ወደ ራፒድ ራይድ ፌርማታ በማሳደግ

## ራፒድ ራይድ ወደ ሬኒየር መምጣት ለምን አስፈለገ?

አሁን ያለው 7 ቁጥር አውቶቢስ 11,000 ተሳፋሪዎችን በየቀኑ ወደ ተለያዩ ትምርት፡ ቤቶች፣ ቤቶችና ፓርኮች በማድርስ በሲያትል ከፍተኛ ቁጥርያለው ተጠቃሚ ከሚያገለግሉ መስመሮች አንዱ ነው፤፤ የ 7 ቁጥር አውቶቢስ መስመር ላይ ያሉ አውቶቢሶች በየ 10 ደቂቃ እንዲመጡ ቢጠበቅም፣ በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ላይ ያለው መጨናነቅ አውቶቢሶች እስከ 40% እንዲዘገዩና እስከ 20% የሚሆን ጊዘ ከ 5 ደቂቃ በላይ ያረፍዳሉ፤፤

ሬኒየር አቨኑ ነጋዴውን ለማገልገል ሲባል ለጭነት መኪኖች የሚሆኑ ሰፊ መንገዶች ቢኖሩትም በከተማው ካሉ መስመሮች ሁሉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ግጭት አለው፤፤ የታቀዱት የራፒድ ራይድ ፕሮጀክቶች አስተማማኝነትና መጓጓዣ ሰዓትን ፐሚያሻሽሉ ብቻ ሳይሆኑ ይሄንን መስመር ለሚጠቀሙ ሁሉ ደህንነታቸውን ያሻሽላሉ፤፤




**Transit Network**

- RapidRide Rainier Line
- Key Connection
- Other RapidRide
- Link
- Seatte Streetcar

**በሬኒየር መስመር ሊካተቱ የሚችሉ ነገሮች**

- ለአውቶቢሶች ቅድሚያ የሚሰጡ አዲስ የትራፊክ መብራቶች
- ቤሌሌክትሪክ ለሚሰሩ አውቶቢሶች አዲስ ወይም የተሻሻሉ ኤሌክትሪክ መሳሪያዎች
- አውቶቢሶች ቶሎ እንዲንቀሳቀሱ ሲባል የአውቶቢስ በቻ መስመሮች ወይም ለነጋዴዎች የተፈቀዱ ቦታዎች እና የአውቶቢስ
- የመንገድ ጥገና
- አዲስ ወይም የታደሱ እግረኛ ማቋረጫዎች
- ለሳይክል ምቹ

## በመላው ሬኒየር አቨኑ መጓጓዣ መፍጠር

ሁሉኑም ተጓዦች የሚጠቅሙ ማሻሽያዎችን ነው የምንፈልገው፤ በእግር ቢጓዙ ወይም አውቶቢስ ቢጠቀሙ፣ መኪና ወይም ሳይክል፤፤ ከራፒድ ራይድ ጋር በተያያዘ በምናደርገው ውይይት ላይ ግጭትን ለመቀነስ፣ ዬውቶቢስ አገልግሎት ለማሻሻል እና ጭነቶች በሬኒየር አቨኑ ላይ እንዲንቀሳቀሱ የምናደርጋቸውን ጥረቶች እናሳውቃለን፤፤ ተጨማኢ መረጃ ለማግኘት ይህንን ይጎብኙ፥ seattle.gov/Transportation/SoutheastSeattle

እስከ ኤፕሪል 8 ድረስ
ሀሳቦን ይንገሩን
have a say
RapidRideRainier.participate.online

**PROGRAM INFORMATION & CONTACT**
Dawn Schellenberg, SDOT RapidRide@Seattle.gov
(206) 684-5189

Seattle Department of Transportation
MOVE SEATTLE
King County METRO
VISION ZERØ
SAFER STREETS FOR SEATTLE

## የራፒድ ራይድ ጠቃሚ ነገሮች

የሬኒየር ራፒድ ራይድ የ 7 ቁጥር አውቶቢሶችን ጥሩ ነገሮችን ይወስዳል፣ ግን በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ምርጥ ወደተባለው አገልግሎት ያድጋል:: በዚህ መስማር ላይ የሚከትሉትን ነግሮች ለመተግበር አስበናል::

**ለአውቶቢሶች ብቻ የተተወ መስመር**
ለአውቶቢሶች ብቻ የተተዉ መንገዶች አውቶቢሶችን ከሌሎች ተሽከርካሪዎች የለያሉ:: በዚህም ፍጥነታቸውና አስተማማኝነታቸው ይጨምራል::



**ከአውቶቢሶች ውጪ መከፈያ ዘዴ**
ከአውቶቢሶች ውጪ መከፈያ ዘዴ ተሳፋሪዎች ለመከፈል የሚቆሙትን ሰልፍ ስለሚያስቀር ፍጥነት ይጨምራል::




**ቀልጣፋ የምልክት መብራቶች**
ለአውቶቢሶች ቅድሚያ የሚሰጡ መብራቶች ለአውቶቢሶች አረንጓዴውን መብራት ቀድሞ በማሳየት ወይም እንደበራ በማቆየት እንዳይዘገዩ ይረዳሉ::



**የተሻሻሉ የአውቶቢሶች ፌርማታዎች**
የራፒድ ራይድ ፌርማታዎች መምጫ ሰዓት ፐሚያሳዩ፣ ትላልቅ መጠለያዎች፣ መብራቶችንና ለሎች መገልገያዎችን::



**ለየት ያሉ አውቶቢሶች**
በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የራፒድ ራይድ አውቶቢሶች ብዙ መያዝ ይችላሉ እንዲሁም ዝቅ ስለሚሉ ለመጫንና ለማውረድ ቀላል ናቸው::



**እግረኛና ብስክሌተኛ ከአውቶቢሶች ጋር ማገናኘት**
በእግረኛ ማቋረጫ፣ በኔይበርሁድ ግሪንወይስ እና የሳይክል መስመር ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ህዝቡን ከራፒድ ራይድ ጋር ያገነኛሉ::



**የመንገድ ጥገና**
አስፈላጊ በሆነ ሰዓት ለአውቶቢሶችና ለመኪኖች ለጥ ያለ መንገድ ለመፍጠር የመንገድ እድሳት ማድረግ



## የፕሮጀክቱ የጊዜ ሂደት




## ገንዘብ

ለራፒድ ራይድ ማስፋፊያ ፕሮግራም በዘጠኝ ዓመት $930 ሚሊዮን ዶላር የሚሰበሰብበት MoveSeattle የተባለ ግብር መሰብሰቢያ ፕሮግራም ከፊሉን ወጪ ይሸፍናል:: ከኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ጋር በመተባበር SDOT የተለያዩ የገንዝብ ድጋፎችንና የትብብር እድሎችን በመፍጠር የግብር ከፋዮችን ገንዘብ ሙሉ ወጪውን እንዲከፈል ለማድረግ ይጥራል::

## አዲስ የራፒድ ራይድ መስመሮች ወደ ሲያትል ይመጣሉ

ፈጣንና አስተማማኝ የአውቶቢስ አገልግሎት ለማስፋት ከ King County Metro Transit ጋር በመተባበር ሰባት አዳዲስ የራፒድ ራይድ መስመሮች በሲያትል ልናስገባ ነው:: ወድፊት በሲያትል የሚዘረጉ የራፒድ ራይድ መስመሮችን በዚህ ገጽ ይመልከቱ፥
seattle.gov/Transportation/RapidRideExpansion.htm

**PROGRAM INFORMATION & CONTACT**
Dawn Schellenberg, SDOT RapidRide@Seattle.gov
(206) 684-5189

Seattle Department of Transportation | MOVE SEATTLE | King County METRO | VISION ZERO SAFER STREETS FOR SEATTLE